# የስድ ገበያ ኢኮኖሚና ልጆቻችን

ሚያዝያ 4 ቀን እሁድ የአውሮጳ አድማጮች በተላለፈው የቀስተ ደመና ሬድዮ ዝግጅት 'የስድ ገበያ ኢኮኖሚ...' በሚል ርእስ አንድ ትችት ተላልፎ ነበር። እንዳጋጣሚ ሆኖ በዚያው እለት ማታ በቢቢሲ ቴሌቪዥን 'ካሚክ ኤይድ' በሚል ፕሮግራም ስለኢትዮጵያ ህጻናት ሁኔታ አንድ አጭር ሪፖርት ቀርቦ ነበር። ይህንን ፕሮግራም ለመመልከት የቻሉ ዜጎች ጧት በሬድዮው ያዳመጡትን ትችት መልሰው ለማስላሰልና በተለይ ደግሞ ጥቂት በወያኔ ዙሪያ የተኮለኮሉ ህብረ ብሄር ገዥዎች በህዝባችን ላይ በመጫን ላይ ካሉት ሥነ ሥርዓት ከተከተሉ የገበያ ኢኮኖሚ ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው የስድ ገበያ ኢኮኖሚ የተባለውን የቀረበውን ትንተና ወቅታዊነት ለመገንዘብ አጋጣሚ እንደገኙ አንጠራጠርም።

ይህ የቢቢሲ ቴሌቪዥን ፕሮግራም የቀረበው ኮሚክ ኤይድ የተባለው ድርጅት በመላ ዓለም ችግረኞችን ለመርዳት የሚያደርገውን ጥረት ለማሳየትና ርዳታም ለመሰብሰብ ነበር። ድርጅቱ በኢትዮጵያም ችግረኛ ህጻናትንም ለመርዳት የሚያስችለው ፕሮጀክት አለው። በፕሮግራሙ የታዩት እናት አባት የሌላቸው ወይም ደግሞ በችግር ብዛት ሊያሳድጓቸው ባለመቻላቸው በረንዳ አዳሪ የሆኑ የ6/7 ዓመታት ጨቅላ ህጻናት ናቸው። ድርጅቱ መጠለያ ስጥቷቸዋል። በዚያ መጠለያ ውስጥ ማደር ይችላሉ። ጧት ጧት ለቁርስ ሰልፍ ይቆሙና አንዳንድ እፍኝ የገብስ ቆሎ ይታደላቸዋል። ድርጅቱ ከዚያ በላይ መርዳት ስለማይችል ለቀሪው የቀን ቁርሳቸው እነዚህን ጨቅላ ህጻናት 'ያገኛችሁትን በልታችሁ ማታ ተመለሱ' ብሎ መንገድ ላይ ይለቃቸዋል።

እነዚህ ህጻናት ማታ ወደ መጠለያዠው እስኪመለሱ ድረስ የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ትክክለኛ አእምሮ ያለውን የማንንመ ዜጋ አንጀት የሚበላ መፍጨርጨር ሲያደርጉ ይታያሉ። አንዳንዶቹ ቡና ከሚጫንበትና ከሚራገፍበት ገበያ የቡና ፍሬ እየለቀሙ እፍኝ ከሞላላቸው ያቺን ለመሸጥ ይለፋሉ። ሌሎች ቆሻሻና ብጥስጣሽ ወረቀት ይሰበስባሉ። ሌሎች ደግሞ በቀጥታ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች እየሄዱ ከቁሻሻ ጋር አብሮ የተጣለ ምግብ እናገኝ እንደሆን በሚል ተስፋ ግማቱንና የዝንቡን ሠራዊት እየተከተሉ ይህም የእለት ጉርስ ከተባለ ለእለት ጉርሳቸው ሲባዝኑ ይታያሉ።

እንዲህ ዓይነቱ አስቃቂ ሁኔታ በሃገራችን ላይ በወያኔ አጋፋሪነት ጥቂት ህብረ ብሄር ግፈኞች የጫኑት ግፈኛ ሥርዓት አንድ ገጽታ ነው። ከስተ ዳመና ሬድዮ የዛሬ ስምንት ወር ስርጭቱን ሲጀምር ከዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ ከብሄሮች እኩልነትና የኢትዮጵያ አንድነት ጋር የማህበራዊ ፍትህ ጉዳይም እጅግ ሰፊ የሆነ የትግል መስካችን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጣችን የሚታወስ ነው።

ይህ የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄ ዛሬም አፍጦና አግጦ ከፊታችን የተደነቀረ ጥያቄ ነው። ይህ በሃገራችን በመንገስ ላይ ያለው የፈትህ መጓደል ጥያቄ አያደርም ቢሆን እየተባባሰና እየከፋ ሄዶ የሃገራችንን ሰላም የህዝቦቿን አንድነትና ወንድማማችነት መቀመቅ ውስጠ በመጨመር አስከፊ አዙሪት ውስጥ የሚከት ካንሰር ነው። አሳሳቢና አንገብጋቢ የሆነውን ያህል ደግሞ ችላ የተባለ የትግል መስክ እንደሆነም ግልጽ ይመስለናል።

ወያኔ ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ ሊሰጠው ሳይሆን ህዝቦችን ከፋፍሎ የግፍ አገዛዙን ለማራዘም ባነገበው የብሄር ጥያቄ ሳቢያ የኢትዮጵያ ህዝቦች መሠረታ የህልውናና የፍትህ ጥያቄ ችላ ተብሏል።

አንዳንዶች ዛሬ ይበልጥ አንገብጋቢ የሆነ የብሄሮች መብት ጥያቄ አለብን፣ ሌሎች ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ እያለብን የማህበራዊ ፍትህን ማዘናጊያ ምን አመጣው ለማለት ይቃጣቸዋል። ግን ልብ ብሎ ለሚመለከት ዜጋ፣ ቆም ብሎ የሃገራችንን የወደፊት እድል ለሚያሰላስል ዲሞክራት እነዚህ የትግል መስኮች የሚተጋገዙ ብቻ አይደሉም። አንዱን ትቶ በሌላው የትግል መስክ፣ አንዱን ትቶ ለሌላው ዓላማ እገፋለሁ ብሎ መግደርደር ራስን ከሁለት ላጣ ጉመንነት እንደ መዳረግ ነው። የብሄሮች መብት እንዲከበር የግለሰቦች መሠረታዊ፣ ሰበአዊና የህልውና መብቶች እንዲረጋገጡ መታገልና ለዚም ትግል በሚልዬን የሚቆጠሩ ዜጎችን ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ አንድነትም የሚረጋገጠው አሁን እንደሚታየው ሁሉም በየብሄሩ ጎራ ለይቶ እየተካተተና የጎሪጥ እየተያየ፣ የብሄሮች ጥላቻ መርዝ ከእለት እለት እየጠጠረ የሚሄድበትን ሁኔታ በማመቻቸት አይደለም። ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የአንድነት ኃይሎች ለብሄሮች መብትና ለኢትዮጵያ አንድነት ዲሞክራሲየዊ መፍትሄያቸውን አንግበው እዚያው በዚያው ደግሞ ከብሄር ማንነት ባሻገር የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ በህልውናቸው ላይ የመጡባቸውን ግፈኛ ሥርዓት በጋራ ትግል እንዲቋቋሙ መንገዱን በማሳየት እንጂ።

ባለፈው ዝግጅታችን ብለን እንደነበረው ችግር ላይ የወደቁ ወዛደሮች ብሄራቸው ሥራ አጥነታቸው ነው። የዘመኑ የወያኔ ባለሃብቶችና ህብረብሄር ግብረአበሮቻቸውም ቢሆኑ ከህብረብሄሩ ድሃና ክልጁ ጉሮሮ ከሚነጥቁ ሃብት ሌላ የሚያውቁት ብሄርም ሆነ ቆመንለታል ሊሉ የሚችሉት ህዝብ የላቸውም። ዛሬም በቢቢሲ ቴሌቪዥን ለተመልካች የቀረቡት ጨቅላ ህፃናት ለኛ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ልጆች አይደሉም።

እጅግ ጨካኝ የሆነ የጥቂት ህብረብሄር ስግብግቦች አረመኔ ሥርዓት የእለት ጉርሳቸውን ከውሻና ከዝንብ እየተሻሙ ለመቃረም የዳረጋቸው የኢትዮጵያ ልጆች፣ የኛ የሁላችን ልጆች ናቸው።

ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ቢያንስ ጽኑ ዲሞክራቶች ነን የሚሉት ክፍሎች ይህንን መሠረታዊ ሃቅ ተገንዝበው በሚልዬን የሚቆጠሩ የሃገራችን ወዛደሮችና ሥራ አጦች፣ መሬት አልባ ገበሬዎችና ተፈናቃይ የመንግሥት ሠቦተኞች፣ ነጋዴዎችና ሌሎችም በተተከለብን ጨካኝ አገዛዝ ሳቢያ ለችጋርና ለውርደት የተዳረጉ ዜጎች በየእለቱ ከሚያደርጉት አስቸጋሪና የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትንቅንቅ የግድ መፀባለቅ አለባቸው። በዚህ መልክ ሚልዬኖች ለህልውናቸው በሚያደርጉት ትግል ከተደባለቁ እዚያው በዚየው ሌሎችን በእርግጥም አንገብጋቢ የሆኑትን የብሄሮች መብትና የሃገራችን አንድነት ጥያቄ የታጋይ ህዝብ አጀንዳ ውስጥጥ እንዲገቡ ማድረግ ይችላሉ። በዚህ መልክ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለእኩልነትና ለአንድነት ወሳኝ የሆነውን አስተዋጽኦቸውን እንዲያበረክቱ ካልታገዙ በየትኛውም መስክ የምናደርገው ትግል የትም የሚደርስ አይሆንም። የኢትዮጵያ ብሄሮች እኩልነት ጉደይ ለነወያኔና መሰል አ ክራሪዎች የመፈንጫ ሜዳ እንደሆነ ይቀጥላል። እንደህ ዓይኦቱ አካሄድ ደግሞ የሃገራችን ዲሞክራቶች በሙሉ የሚመኙትን በእኩልነት ላይ የተመረኮዘ አንድነት ጉዳይ ከማይገብረው የሚልዬኖች ክንድ ፈልቅቆ አውጥቶ በሆዳቸው ብቻ ለሚያስቡ፣ ለሃገርም ሆነ ለወገን ደንታ ለሌላቸው እፍኝ ጸረ ህዝቦች የማስረከብን ያህል አደገኛ ቁማር ነው።